# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**ወያኔ በርሀብ የተጠቁ ዜጎች እንዳይታዩ አድራሻቸውን መደበቁ ተጋለጠ**

**ከምግብ እርዳታ ይልቅ የሲሚንቶ ጭነት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባም ታዘዘ፤**

**የተሰጋው የጎርፍ አደጋ ተከሰተ አንድ ቀበሌ ሙሉ ለሙሉ ወደመ፤**

የድርቅ አደጋው እየተባባሰ መሄዱ በተረጋጋጠበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን በድርቅ የተጎዱትን ዜጎች አድራሻ ጭምር እየደበቀ እና የማስመሰያ የድረሱልን ጥሪ እያቀረበ መሆኑ በመላ ሀገሪቱ ህዝቦች ዘንድ እያነጋገረ መሆኑ ታወቀ፡፡

በምስራቅ አፍሪካ በተለይ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በርሀብ እና በችጋር የተጠቃባት ሀገር መሆንዋን የዓለም አቀፍ ረድኤት ድርጅቶች ባስታወቁበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን የርሀብተኛ ወገኖችን አድራሻ እየሸሸገና እየደበቀ መሆኑን ከደቡብ እና ከሱማሌ ክልል የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች በቡድን በመሆን ወደ አካባቢው በመጉዋዝ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ለማየት እና ለዓለም ህብረተሰብ ጥሪ ለማቅረብ በሄዱበት ወቅት የወያኔ ቡድን ካድሬዎች በሱማሌ ክልል ውስጥ ያሉትን ረሀብተኞች የሱማሌ ተወላጆች እንጂ የኢትዮጵያ ዜጎች አይደሉም በማለት የዋሹ ሲሆን በደቡብ ክልል ያሉትን ደግሞ የረድኤት ሰራተኞቹ ወደ ስፍራው እንዳይደርሱ የጎርፍ አደጋ ስላለ እቦታው መድረስ አይቻልም በማለት ሲያስፈራሩዋቸው እንደነበረ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

እብሪተኛውና ዘረኛው የወያኔ ቡድን የርሀብተኛ ዜጎች አስፈላጊው እርዳታ እንዳያገኙ እየደበቀና እየዋሸ ከመሆኑም በላይ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በአስቸኩዋይ እንዳይደርስ እየተከላከለ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ከዜጎች ህይወት ማዳን ይልቅ የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም የሚሆናቸውን ስልቶች ብቻ እየፈለጉ ባለበት በዚህ ግዜ ከ6 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሞት እና በመኖር መሀከል እየዋለሉ ከመሆኑም በላይ ለግዜው ቁጥራቸው ያልታወቁ ዜጎች እየሞቱ ቀባሪ አጥተው እንደሚገኙ የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች በምስል አስደግፌው ለዓለም ማህበረሰብ ከበተኑት መግለጫ ለመረዳት ተችሎዋል::

በአሁኑ ሰዓት በምስራቅ አፍሪካ ከ12 ሚሊዮን በተለይ ከኢትዮጵያ ደግሞ 6 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በርሀብና በቸነፈር አለንጋ እየተገረፉ ብዙዎቹ ወደ ሞት እየተጉዋዙ ባለበት እና የረድኤት ድርጅቶች የድረሱልን ጥሪ እያቀረቡ ባለበት ሰዓት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ግን እጃቸውን አጣምረው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎዋል::

ሰሞኑን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብና የእርሻ ድርጅት ባቀረበው ጥሪ መሰረት በምስራቅ አፍሪካ በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው ርሀብ ግዜ የማይሰጥና እጅግ የከፋ ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ሁሉም ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የበኩሉን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል በማለት ጥሪ እያቀረበ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን ግን የርሀብተኛውን ህይወት ከመታደግ ይልቅ ለኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ የሚውል የሲሚንቶ ምርቶችን ከውጭ ሀገር አስመጥቶ በሺህዎች የሚቆጠሩ የጭነት መኪኖች ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ እያጉዋጉዋዙ መሆኑ ታውቆዋል::

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት በጣሊያን ሮም ከተማ ባደረገው አስቸኩዋይ ስብሰባ ላይ በተለይ መንግስት አልባዋ ሱማሌና በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው አስከፊና አስደንጋጭ ርሀብ አጣዳፊ መፍትሔ ካልተፈለገለት እጅግ ከባድ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ገልፆ የዓለም ማህበረሰብ አጣዳፊ ድጋፍ እንዲያደርግለትም ተማጽኖ አቅርቦዋል::

የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የድረሱልን ጥሪ እያቀረቡ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድንም ለማስመሰል እና አልኩ ለማለት ያህል ጥሪ ቢያቀርብም በተግባር ግን እየሰራ ያለው በተቃራኒው እንደሆነ እየገለፁ የሚገኙት የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች በአሁኑ ሰዓት ዜጎች በእርዳታ እጦት እየሞቱ ባለበት ሰዓት ለሲሚንቶ ቅድሚያ ሰጥቶ እያጉዋጉዋዘ መሆኑን በመቃወም እያጋለጡት ይገኛሉ::

በአሁኑ ሰዓት በጅቡቲ ወደብ የምግብ እርዳታ የጫኑ መለስተኛ መርከቦች ቆመው ቢገኙም የወያኔ ቡድን ግን በቀን ከ500 መኪኖች በላይ የሲሚንቶ ጭነት እያስጫነ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ ከመሆኑም በላይ ሲሚንቶ ጭነው የመጡት መኪኖች አራግፌው እንዳይመለሱ ግዜ እየፈጀ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሎዋል::

በርሀቡ ምክንያት ሰውነታቸው ደቅቆ መላወስ አቅቶዋቸው ትላልቅ ጭንቅላቶቻቸውን መሸከም ያልቻሉ ዜጎች ቁጥር እጅግ የበዙ መሆኑን ያጋለጡት የረድኤት ድርጅት ሰራተኞቹ ወያኔ ለነዚህ ዜጎች አጣዳፊ የምግብ እርዳታ ከማቅረብና ህይወታቸውን ከመታደግ ይልቅ ለራሱ ካድሬዎች

መኖሪያ የሚሆን የኮንዶሚኒየም ቤቶችን ለመገንባት ሲል ሲሚንቶ እያጉዋጉዋዘ መሆኑ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉ እነዚሁ የድርጅቱ ሰራተኞች በቁጭት ይገልጻሉ::

ከመንግስት አልባዋ ሱማሊያ ባልተሻለ ሁኔታ በኢትዮጵያም የተራቡ ዜጎች እርዳታ ተነፍጎዋቸው አይናቸው እያየ.....ጆሮዋቸው እየሰማ..... ምግብና ውሀ እያሉ ......የወገን ያለህ ብለው እየተማጸኑ መሆናቸውን ከስፍራው የሚደርሱ ዘገባዎቸ ይጠቁማሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከድርቁ በተጉዋዳኝ የጎርፍ አደጋ በሀገሪቱ ሊከሰት ይችላል በሚል የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስጋታቸውን ሲገልፁ የነበረ ሲሆን ስጋታቸው እውን ሆኖ ሰሞኑን በኢትዮጵያ የጎርፍ አደጋ ማድረሱ ታወቀ::

እሁድ ዕለት ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም በደቡብ ክልል በዱራሜ አካባቢ በተከሰተ የጎርፍ አደጋ አንድ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሙሉ ለሙሉ የወደመ ከመሆኑም በላይ በሺህዎች የሚቆጠሩ የቤት እንሰሳት በጎርፉ የተወሰዱ ሲሆን ቤት እና ንብረቶቻቸው ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጭ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

የዚሁ ቀበሌ ነዋሪዎች በጎርፍ አደጋው ሳቢያ ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ከመሆኑም በተጨማሪ መንገዶች እና ድልድዮች እንዲሁም መኖሪያ ቤቶች በጎርፉ በመወሰዳቸው ወደ ስፍራው የሚያገናኝ መንገድ ሙሉ ለሙሉ መቁዋረጡንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

አደጋው ሳይደርስ በሰው ህይወት እና ንብረት ላይ ጉዳት ሳያስከትል አስቀድሞ መከላከል እንዲቻል የዓለም አቀፍ ተቁዋማት ጥሪ ቢያቀርቡም የወያኔ ቡድን ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ዝምታ በመምረጡ የተሰጋውና የተፈራው ነገር ደርሶ ችግሩ ሊከሰት እንደቻለ ያጋለጡት እነዚሁ የዓለም አቀፍ ድርጅት ሰራተኞች አሁንም በቅርቡ በተለያዩ አካባቢዎች ተመሳሳይ ችግር ደርሶ ለብዙ ሺህ ዜጎች ሞት እና መፈናቀል ሊከሰት ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ገልፀዋል::

በደቡብ ክልል ውስጥ በተከሰተው በዚሁ የጎርፍ አደጋ አንድ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ከጥቅም ውጭ ከመሆኑም በተጨማሪ በመቶዎች የሚቆጠሩ አቅመ ደካማና ህፃናቶች በጎርፉ ተወስደው በአካባቢው ሰዎች ርብርብ የተረፉ ቢሆንም ለከፋ አደጋ እንደተዳረጉና በየህክምና ጣቢያዎች እንደገቡም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በጎርፉ አደጋ ለተጠቁት ዜጎች እርዳታ እንዳይሰጥ መንገዱ ተደርምሶ መገናኛ መስመር የተቁዋረጠ በመሆኑ ዜጎች ለቀናት በርሀብ ውስጥ የሚገኙ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በሺህዎች የሚቆጠሩ የቤት እንሰሳቶች በጎርፉ ተወስደው በየሜዳው ላይ በመሞታቸው የተነሳ ጸሐይ በወጣበት ወቅት አካባቢው በመጥፎ ሽታ የተበከለ ሲሆን ከርሀቡ ጋር ተደማምሮ ህዝቡ ለከፋ ችግር ተዳርጎ እንደሚገኝም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ዛሬ ከ6 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የመላስ የሚቀመስ አጥተው በሞት አፋፍ ላይ ባሉበት ወቅት .......በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩት በጎርፍ አደጋ ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው ባሉበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት በሚስቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም ሀብት እያግበሰበሱ የሀገሪቱዋን አንጡራ ሀብት እየቦጠቦጡ ዜጎች በርሀብ አይናቸው እያየ በመሞት ላይ ይገኛሉ::

ትልቁና ዋነኛዋ የሀገር ሀብት በዝባዥ የሆነችው የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ከዚህ ቀደም በፈጸመችው ዝርፊያ በሀገሪቱ የጸረ ሙስና ኮሚሽን በተባለው መስሪያ ቤት ተከስሳ ለፍርድ እንድትቀርብ ተብሎ በወቅቱ ኮሚሽነር በነበረችው እንወይ ገብረመድህን ትዕዛዝ ክሱ ቢጀመርም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ግን ሚስቱን ለማዳን እና ገመናውን ለመሸፈን ሲል እንወይን ከስልጣን አብርሮ ክሱ እንዲቆዋረጥ መደረጉን የሚያስታውሱት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ዛሬ ችጋር እና ርሀብ በሀገሪቱ ስር ሰድዶ ባለበት ሰዓት ከህዝብ የዘረፉትን ሀብት በውጭ ባንኮች እያከማቹ ለተረጂው ህዝብ የተላከው የምግብ እርዳታ እንዳይደርስ ሌላ ችግር እየፈጠሩ መገኘታቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው ሲሉም በቁጭት ይገልጻሉ::

በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ቦታዎች በውጭ ሀገር በሚገቡ ቆርቆሮዎች ደረጃውን የጠበቀ አጥር እንዲሰራ ብሎ መመሪያና ደንብ ኩማ ደመቅሳ ያወጣ ሲሆን ይህንን ቆርቆሮ የመለስ ሚስት የሆነችው አዜብ መስፍን ብቸኛ አስመጪ በመሆን ከዋጋ በላይ ስንጥቅ ትርፍ እያተረፈች በኮንስትራክሽን ስራ ላይ በተሰማሩና በባለሀብቶች ላይ እየተጫወተች ከመሆኑም በላይ ለተረጂው ህዝብ ከጅቡቲ ወደብ መግባት የሚገባውን የእርዳታ እህል ከማጉዋጉዋዝ ይልቅ አዜብ ያስመጣችው የግንባታ ቁሳቁሶች በቅድሚያ እንዲጫኑ እየተደረገ መገኘቱንም እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ነጋዴውን ከ15 እጥፍ በላይ ግብር ክፈል ተብሎ የስንግ ከመያዙም በተጨማሪ በአዲሱ የንግድ ምዝገባ ደግሞ አንድ ነጋዴ አንድ ዓይነት ስራ ብቻ እንዲሰራ በተደረገበት በዚህ ግዜ ወ/ሮ አዜብ ግን በመኪና አስመጪና ሻጭነት፤በአበባ እርሻ፤ በቡና ላኪነት፤በኮንስትራክሽን ስራዎች ወዘተ...... ወዘተ..... ላይ እንደልብዋ እየጨፈረች የሀገር እና ህዝብ ሀብት እያግበሰበሰች ከመሆኑም በላይ በኤች አይ ቪ ኤድስ በተጠቁ ወገኖች ስም የሚመጣውን ዶላር በግል ካዝናዋ በውጭ ሀገር እየከመረች ከመሆኑም በተጨማሪ በርሀብ ለተጠቁ ወገኖች የሚመጣውን አልሚ ምግብ እየቸበቸበች መሆኑንም አጋልጠዋል::

ዜጎች ግን የሚቀምሱት አጥተው በተቀመጡበት እየሞቱ...... ቀባሪ አጥተው ባሉበት በዚህ ግዜ የወያኔው መሪ መለስ የረድኤት ድርጅቶች የሰጡትን የምግብ እርዳታ እንኩዋን ለተራቡት ወገኖች እንዳይደርስ ሲሚንቶ ማመላለሱ በዜጎች ላይ የሞት ፍርድ መፍረዱን ያሳየ የጭካኔ እርምጃ መውሰዱን ያመላከተ ውሳኔ መሆኑ የረድኤት ድርጅት ሰራተኞች እየተናገሩ ይገኛሉ::

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ በርሀብ እና በችጋር ተጠቅተው የተቀመጡ ወገኖች አስቸኩዋይ እርዳታ እንዳይሰጣቸው የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት አድራሻቸውን ከመሸሸጋቸውም በተጨማሪ እድል ቀንቶዋቸው ከሞት ተርፈው ወደ መሀል ሀገር በመሰደድ ላይ ያሉትን ዜጎች ቅልብ የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ እና ተወርዋሪ ፖሊስ አባላት ከየመንገዱ እያፈሱ ወዳልታወቀ ስፍራ እየወሰዱዋቸው መሆኑንም ከሚደርሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

የወያኔ ቡድን የዜጎችን ህይወት ከማዳን ይልቅ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ በማድረግ በሺህዎች የሚቆጠሩ ወታደሮችን እና ተወርዋሪ ፖሊሶችን አሰልጥኖ እያስመረቀ እንደሚገኝም ታውቆዋል።

ለወያኔ አናጎበድድም...... ለወያኔ መሳሪያ አንሆንም በማለት በመላ ሀገሪቱ ወጣቱ ለውትድርና አንመለመልም ሲል ለልዩ ኃይል በሚል የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንሰጣችሁዋለን እያሉ እየደለሉና እያታለሉ መልምለው በምስጢር በጦላይ ታደራዊ ማሰልጠኛ ያሰለጠኑዋቸውን 4 ሺህ የፌዴራል ፖሊስ ተወርዋሪዎችን ማስመረቁ ታውቆዋል።

ርሀብ በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ አስጊ ደረጃ ላይ ደርሶዋል እየተባለ የዓለም ህብረተሰብን እያነጋገረ ባለበት በዚህ ግዜ ሐምሌ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በጦላይ ለወራት ሲሰለጥኑ የነበሩ ተወርዋሪ ፖሊሶችን ያስመረቀ ሲሆን በምረቃው ላይም የተገኘው ከውህዳኑ እራሱን ገንጥሎ ይቅርታ ጠይቶ ወደ መለስ ቡድን የተቀላቀለው ሀሰን ሽፋ መሆኑም ታውቆዋል።

በዚሁ ምረቃው ላይ የክብር እንግዳ ሆኖ የቀረበው ይሄው ወላዋዩ የህወሀት ኢህአዴግ ባለስልጣን ሀሰን ሽፋ በወቅቱ ንግግር ሲያደርግ ወሳኝ የሆነ ፍልሚያ ይጠብቃችሁዋልና ተዘጋጁ ሲል ያስጠነቀቀ ሲሆን በርሀብ ለተጎዱት ትደርሱላቸዋላችሁ ከማለት ይልቅ በዜጎች ላይ አፈሙዝ ወድረው እንዲዘምቱባቸው የሚያዝዝዝ መመሪያ ማስተላለፉም እያነጋገረ ይገኛል።